# ታሪክን አሻጋሪ ፈዋሽ መዳፎች

በኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት የአብያተ መጻሕፍት መረጃ ሀብቶች አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ ዘርፍ የሆነው የመረጃ ሀብቶች ደህንነት ጥበቃና እንክብካቤ ዴስክ እንደስያሜው ተቋሙ በአዋጅ፣ በስጦታና በግዢ የሚሰበስባቸውን የመረጃ ሀብቶች ደህንነታቸውን አስጠብቆ የታመሙትን አክሞ ለቅድመ ጥንቃቄ በእንክብካቤ አደራጅቶ ወደ ተቋሙ አገልግሎት መስጫዎች የሚያስተላልፍ ክፍል ነው፡፡

በዚህ የመረጃ ሀብቶች ደህንነት ጥበቃና እንክብካቤ ዴስክ ያሉ ባለሙያዎች የእነሱን ሙያዊ ሥራ ያገኙ ዘንድ የመጡላቸውን ጋዜጦች በራሳቸው  እትም በቀናቸው፣ በወራቸው አስተካክለው በክር በመስፋት የጥራዙን የመጀመሪያ ሥራ ከከወኑ በኋላ አቡጀዲ በማድረግ ኮላ ይቀባሉ፡፡ ይህ ባለበት ልባስ ወይም ሽፋን የመምረጥና የማዘጋጀት ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህ ጊዜ ቢያንስ ለሁለት ቀናት የተቀባው ኮላ እስኪደርቅ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ በመቀጠል ይታፈፋል ቀጥሎም ቦርድ እንዲሁም ቴላ ይቆረጣል፡፡ ከእነዚህ በኋላም አፍንጫና  ውሻል  ተሰርቶለት አንድ ላይ ተደርጎ ከተገጠመ በኋላ ሙሉ በሙሉ እስኪይዝ አስፈላጊው ሂደት ተደርጐ ለሁለት ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በመቀጠል በክርና መርፌ በእጅ በመስፋት ተጀምሮ በተለያዩ የሽፋን ቀለማት ወደተላበሰ የሚያምር ጠንካራ ውብ ጥራዝ የተቀየረው የጋዜጣ ወይም የመጽሔት ስብስብ የሚያስፈልገው የስራ እርማት ካለ በሚል የመጨረሻው የስራው መቋጫ የሆነው መመርመር የተሰኘውን ክዋኔ ባለሙያዎቹ ይተገብራሉ፡፡ ይህም በስራው መሐል የተጣበቁ ገፆች ወይም አንዳች እንከን ካለ ወደ አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ለማስተካከል ያስችላል፡፡

የክፍሉ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት ብዙ ጊዜ ጋዜጣና መጽሔቶች የአንድ ወር እትም በቀናቸው ተስተካክለው አንድ ጥራዝ ተደርገው የሚወጡ ሲሆኑ ይህ ስራ ቀደም ብሎም ስለነበረና ለዘመናት ስለተሰራ አገልግሎት ላይ ውለው ጉዳት ደርሶባቸው ለጥገና ከሚመጡት በቀር አብዛኛዎቹ አዲስ እንደመሆናቸው ስራውን ቀላል የሚያደርገው ሲሆን ከመጻሕፍት ጋር በተገናኘ ግን በተለይ የድሮ መጻሕፍት ሲጠገኑ የቀድሞውን ያህል ውበትና በነበሩበት ልክ ለመመለስ በጥቂቱ ያስቸግራል፡፡

ከመጻሕፍት ጋር በተያያዘ ባለሙያዎቹ በስራቸው የታዘቡት ነገር ተጠቃሚዎች የመረጃ ሀብቶች ላይ ማለትም ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍት ላይ የማይለቁ ጽሑፎችን ከመጻፋቸው በላይ የተወሰኑ ገፆችን ገንጥለው እንደሚወስዱ እና በቅርብ ለህትመት የበቁ መጻሕፍትም እንደ አዲስነታቸው ሳይሆን በአጭር ጊዜ ገፆቻቸው ተበታትነው ለጥገና እንደሚመጡ ይህም በህትመት ቤት ያለው የአሠራር ክፍተት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ትውልድ በቂና የተሟላ መረጃ ያገኝ ዘንድ ወደ ቀጣዩም ትውልድ እንዲተላለፍ በልዩ ፍቅር አበቃለት የተባለን የበታተነ የወረቀት ክምር ነው የሚባልን የመረጃ ሀብት ሙያዊ ዕውቀታቸውን በጥበባዊ እጆቻቸው ፈውሰው ወደነበረበት የመጽሐፍ፣ የጋዜጣ፣ የመጽሔት ገፅታ የሚመልሱ የተቋሙ ሀኪሞች ማህበረሰቡ በመረጃ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ የኃላፊነት ስሜት ይሰማው ከሚለው መልዕክታቸው ጐን ለጐን ራሳቸውን በዘርፉ ከልምድ በላይ በከፍተኛ ትምህርት አሳድገው ለማገልገል ፍላጐታቸው ከፍ ያለ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት የመረጃ ሀብቶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ለሚሰራው ሥራ የጀርባ አጥንት የሆነው የመረጃ ሀብቶች ደህንነት ጥበቃና እንክብካቤ የስራ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎት በተቋሙ ብቻ ከመወሰን አልፎ ለይርጋለም የህዝብ ቤተመጻሕፍት ይህ ሙያዊ ግልጋሎት ድጋፍ መደረጉ ተቋሙ ከራሱ አልፎ ከሰራቸው የመረጃ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባራት እንደ አንድ የሚታወስ ነው፡፡